# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 1 ቁጥር 1 መስከረም ፳፰ ቀን ፪ ሺህ ፱

## የወያኔ መቃብር ከጨፈጨፋቸው የኢትዮጵያ ልጆች መቃብር ሥር ይሆናል

**ዳውን Down ወያኔ፤ እፎይ እንዲል ወገኔ**

**ዳውን Down ህወሀት፤ ለኢትዮጵያ አንድነት**

**ዳውን Down ቲፒኤልኤፍ፤ ሰንደቃችን እንዲል ከፍ**

**ዳውን Down ኢህአዴግ፤ ኢትዮጵያን እንታደግ**

መስከረም 22 ቀን 2009 ዓ.ም. በኦሮሞ ብሔረሰብ ዘንድ በየዓመቱ የሚከበረውን ኢሬቻ በመባል የሚታወቀውን የምስጋና በዓል ለማክበር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ደብረዘይት/ቢሾፍቱ እሚገኘው ሆራ ሀይቅ በመገኘት በደማቅ ሁኔታ በማክበር ላይ ነበሩ።

ወንዶቹ እንደ ባህላችን ነጭ እጀ ጠባብ፣ በላዩ ላይ ህብረ ቀለም ወይም ደማቅ ሰደሪያ ተላብሰው፤ ሴቶቹ ነጭ ጥበብ፣ የግር አልቦ፣ በክንዳቸው አምባር፣ በጣታቸው የብር ቀለበት፤ ወንዱ እንደ አርቲ ሴቷ አደስ አደስ እያሉ፣ አዛውንት በነጩ እጀ ጠባብ ላይ ጃኖ ተላብሰው፤ ሳር ነጭተው፣ ቄጤማ ቆርጠው፣ የአደይ አበባ ይዘው፤ ያለፈውን አልፈው፡ ዛሬ ላይ ደርሰው፡ ካለፈው፡ ከዛሬ የተሻለን ነገን ለማግኘት በተስፋ፡ ፈጣሪያቸውን ለማመስገን፡ ለግልም ንስሀን እያሰቡ፡ ለፈጣሪያቸው ምስጋና ሊያቀርቡ፡ በአምልኮት እቆሙበት ሆራ ደብረዘይት፣ ሆራ ቢሾፍቱ ደምቃ ሳትጠግብ፣ ጨለማ ወረሳት። በዓሉን ድምቀት የሰጡት እናቶች፣ አባቶች፣ የአደይ አበባ ሕፃናት፣ የመስከረም ወጣቶች ችቧቸው ጥይት ሆነ፤ የመስከረም ብርሃን በጭስ ተዋጠች። ጆሮዎች ዋይታ፣ ለቅሶ፣ ጩኸት፣ እሪታ ተቀባይ ሆኑ። ሆራ በልጆቿ ደም ቀላች። እግዚሆ! አምላክ ሆይ የሰው ልጅ ጭካኔ አሸነፈህ ሆይ? እስኪያሰኝና ለማመን በሚያቅት መልኩ ተደረገ። እውነት ሆነ። አምላካቸውን በመንፈስ ሊነጋገሩ ኤሎሄ ያሉ ልጆቹ ነፍሳቸው ተላከለት። ኢትዮጵያ ለልጆቿ ዳግም ሳይሆን ደጋግማ አለቀሰች!

በባዶ እጁ ያለ ሕዝብ ላይ ጥይትና አስለቃሽ ጋዝ በመልቀቅና በማስበርገግ በትንሹ ለ600 ሰው ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው የወያኔ መንግሥት ተጠያቂ የሚሆንበት የግፍ ግድያ። "እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሰን" ብሎ ያልጨረሰን ሕዝብ ገደል ከቶ፣ በጥይት ቆልቶ ብሔራዊ ሀዘን የሚያውጅ ገድሎ ቀባሪ መንግሥት ወያኔ/ኢሕአዴግ።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች! ለወያኔ የሕዝብ ልጆችን ደም መጠጣት አዲስ አይደለም። የመስከረም 22ቱ 2009 ዓ.ም. ዕልቂት ለወያኔ ገዳይነት የመጀመሪያው እንዳልሆነ ሁሉ ትግሉ በሕዝብ ድል አድራጊነት እስኪጠናቀቅ የመጨረሻው አይሆንም። ኢሬቻ በዓል ላይ የፈሰሰው የንጹሃን ደም የወያኔ መቀበሪያው ይሆናል። በዕለቱ ባህሉን ለማክበር ወጥታችሁ ለተሰዋችሁ የኦሮሞ ልጆችና ሌሎች ወገኖቻችን የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለጽን ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጅ ዘመዶቻቸውና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ "እግዚአብሔር መጽናናትን ይስጥልን" እንላለን ከ"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"።

ወያኔ ገና አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ በየአካባቢው በደረሰበት ተቃውሞ በማስበርገግ ለማስቆም ሥልጣን በያዘ ሳምንታት ውስጥ በአዲስ አበባ በተደረገ ሰልፍ አሥራ አንድ ወጣቶችን ገድሏል። በየጊዜው ያፈናቸው፣ በዱርዬ፣ በመኪና አደጋ፣ በድብደባ፣ ወዘተ የሞቱ እያስመሰለ የገደላቸው በርካታዎች ናቸው። የኤርትራን መገንጠል ተቃውመው በ1983 ዓ.ም. ሠልፍ የወጡ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ውስጥ ጩቤና መሣሪያ የታጠቁ አስርጐ አስገብቶ "እርስ በርሳቸው ተጋደሉ" በማለት የበርካታዎችን ሕይወት ቀጥፏል። ከምርጫ 1997 ዓ.ም. በፊት እጅግ በርካታ ዜጎችን በመላዋ የሀገሪቷ ክልል የወያኔ አገዛዝ ገድሏል።

በዘረኝነቱም እንጊድ ከተባለ በበደኖና በአርባ ጉጉ የተካሄዱ ጭፍጨፋዎች ተጠያቂው በዋና ነት ወያኔ ነው። በምሥራቅ ኢትዮጵያ በአሸባሪነት ስም በጅምላ የፈጃቸው የኦጋዴን አካባቢ ሕፃናትንና ወጣቶችን ጨምሮ እናትና አባቶች አጽም ዛሬም ይጮሃል። በሃይማኖትም በኩል በጅማና በሌሎች አካባቢዎች የተካሄደው እልቂት ተጠያቂው ወያኔ ነው። 1997 ዓ.ም. ምርጫን አስመልክቶ ከ12 ዓመት ሕፃን ጀምሮ እስከ አዛውንት ለተካሄደው በትንሹ የ196 ወገኖቻችን እልቂት ተጠያቂው ወያኔ ነው። ይህ ሀሃዝ በየገጠሩ፣ በየክፍላተ ሀገሩ ያሉትን ሳይጨምር ነው።

ምርጫ 97ትን አስከትሎ የደቡብ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ጀግንነትና የከፈሉት መስዋዕትነት ከቶም ሊዘነጋ አይገባም። ከነኮሳሳ ቤታቸው በፈንጂ ያጋያቸው ወያኔ ነው። የፕሮፌሰር አሥራትን እንቅስቃሴ አስከትሎ ያሰጋኛል ያለውን የደብረብርሃን፣ ሸንኮራ፣ መንዝና፣ ተጉለት ነዋሪ ላይ መትረየስ ያርከፈከፈው ወያኔ ነው። ያላቋረጠው የጋምቤላ አካባቢ ኅብረተሰብ ፀረ-ወያኔ ተጋድሎ በርካታዎችን ለሞት የዳረገው የወያኔ ጥይትና ፈንጂ ነው።

በስደቱም ዓለም በተለይ በዓረቡ ዓለም ሆን ተብሎ እየተጋዙ የሚሸጡ ወገኖቻችን የወያኔና የባዕዳን ጠላቶቻችን ጥምር ሤራ ነው። ከዚህም አልፎ እየታነቁ ሲታረዱ የነበረው የቅርብ ጊዜ አሳዛኝና አስለቃሽ ትርይት ላይ ሲያላግጥና ሲያሾፍ የነበረው ወያኔ ነው።

በእስላሙ ኅብረተሰብ ዘንድ የተነሳውን "ድምፃችን ይሰማ" ንቅናቄ ለማፈንና ለማኮላሸት በርካታዎችን በየእሥርቤቱ በማጎር እያሰቃየ ያለው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ነው።

በቅርቡ በዋልድባ ገዳም በተነሳው የአካባቢ ጥያቄ መነኮሳትን ሳይቀር ደብዛ ያጠፋውና የቀበረው ወያኔ ነው። በወልቃይት ይገባኛል ጥያቄ ነዋሪውን እያፈናቀለና እያሰቃየ ወደሌላ አመጽ የቀሰቀሰው ወያኔ ነው። በቀሰቀሰው እሳት ሲለበለብም ጉልበቱን ተጠቅሞ በርካታዎችን የፈጀውና እየፈጀ ያለው ወያኔ ነው። ወያኔ በለኮሰው የዘረኝነት ፖሊሲ ዛሬ እየተርገበገበ ይገኛል። የኢትዮጵያን ልጆች እርስ በርሳቸው ለማባላት የሸነሸነው የዘር ተንኮል እራሱ ላይ እያነጣጠረ የኦሮሞ ልጆች "መብታችን ይከበር" ጥያቄን ለማዳፈን ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ቤታቸውን መቃብርና እስር ቤት ያደረገው ወያኔ ነው።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

ዛሬ ስለ ወያኔ ገዳይነት፣ እጅግ በጣም ተንኮልና መሠሪ አካሄድ "ለቀባሪው አረዱት" እንዳይሉ ለታሪክ ዘገብነው እንጂ የገፈቱና የመከራው ቀማሽ መች ተፃፈና፣ መች ተነካና እንደሚባል እርግጠኞች ነን። ፉከራ ሳይሆን ዛሬ ወያኔ በቅቶታል የሚባለው በራሱ አባባል መቶ በመቶ ሕዝብ በቃኝ፣ አልገዛም፣ ወያኔ ይውደም! ዳውን Down ወያኔ! ብሎ ከዳር እስከዳር ስለተነሳ ነው።

ዛሬ ሕዝባዊውን ዓመጽ ያቀጣጠለው እጅግ አደገኛው የወያኔ መሠሪ ተንኮል እያንገፈገፈው ያለው ሕዝብ የመጨረሻ ድምጽ ነው። የችግር፣ የረኀብ፣ የእሥር፣ የግድያ፣ የስቃይ፣ የመፈናቀል፣ የበሽታ፣ ኧረ የስንቱ ውጤት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ነውና ዛሬ ሕዝብ በወያኔ ላይ ተነስቱዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ አገዛዝ ጀምሮ ለ14 ዓመት ያየውን መከራ በአገኘው ዕድል ተጠቅሞ በምርጫ ወያኔን ዘርሮታል። ሆኖም በፖለቲከኞቹ ደካማ ጎን የገባው የመለስ አስተዳደር የነበረውን እንዳልነበረ ቀይሮ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጆ፣ 196 ወገኖችን ገድሎ ያንን ቀን ሊያልፈው ችሏል። ታጋሽና መከራ ቻይ የሆነው ሕዝባችን በእጁ የገባው ድሉን ከተቀማ በኋላ አቅጣጫው ግራ ቢለውም አላቀረቀረም። በአንድ በኩል የወያኔን የሸንገላ አካሄድ እየታዘበ ሲያዘግም ኖሯል። ሕይወቱ፣ መኩሪያው፣ መከታው ነውና ዐባይ ሲነሳ ክብሩ እንደተነካ የሚቆጠቁጠው ሕዝባችን ለዐባይ ግንባታ ወያኔ ጠየቀ ብሎ ወደ ኋላ አላለም። እናቶች ከመቀነታቸው፣ አባቶች ከውስጠኛው ኪሳቸው፣ ሕፃናት ከዳቦአቸው፣ ወጣቶች ከጉርሻቸው ሳይቀር "ዐባይ ያገር ሲሳይ" ብለው ለግሰዋል። በወያኔ ምላሻቸው ግና ንቀት፣ ትዕቢት፣ ማላገጥ፣ ማንገላታት፣ ማፈናቀል፣ መታሠር፣ መገረፍ፣ መገደል ወዘተ መሆኑ የየዕለት ሂደቱ እንደነበር መስካሪው እራሱ ሕዝቡ ነው።

ይህ ዓመት ከዓመት እያስቆጠረ ዛሬ ላይ የደረሰው 25 የግፍ ዓመታት ሊያበቃ ይገባዋል። ዛሬ ወያኔን እያስፈቀደ ሰልፍ ይወጣ የነበረው ሕዝባችን መብቱን ለማስከበር ከገዳይ ፈቃድ እንደማያስፈልገው ተገንዝቧል። ሠልፍ በወጣ ቁጥር የወያኔን የፈጠራ ባንዲራ ይዞ ይወጣ የነበረው ሕዝባችን ዛሬ ዘላለማዊውን የኢትዮጵያዊነቱን መገለጫ ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለበና እየሰቀለ ማንነቱን እያሳየ ነው። ዛሬ ሕዝባችን የወያኔን አፋኝ ሕገ መንግሥት ከማንም በበለጠ ተረድቶና ተገንዝቦ "ወያኔ ይውደም፣ ዳውን ዳውን ወያኔ!" እያለ ነው። እጆቹን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ መብቱን የለመነው ሕዝብ ለሚሰጠው ምላሽ ማንነቱን የሚያሳይበት ቀን

እሩቅ አይሆኑም። ፋሽስት ጣሊያንን ያርበደበዱ እጆች ሥራቸውን የጀመሩ ለታ ወይኔ ለወያኔ። ወደ ላይ የለመኑ እጆች ወደፊት የተዘረጉ ለታ መግቢያም አይገኝ። ለ25 ዓመት በደንብ ያወቀው ጠላቱ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ ለራሱ ለሀገሩ ተነስቷል። እናም ሕዝባዊ ትግሉ በወያኔ መጠገን ሳይሆን መውደም መጠናቀቅ እንደሚገባው "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" በሚገባ ልናስገነዝብ እንወዳለን።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

በአሁኑ ወቅት በመላ ኢትዮጵያ ማለት ይቻላል እየተቀጣጠለ ያለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አጢኖ መጓዝ ይኖርበታል እንላለን፦

***የትግሉ መቀናጀት፦*** ወያኔ በዘረጋው የዘር ወጥመድ ላለመጠመድ ጥንቃቄ ማድረግና የኦሮሞው፣ የአማራው፣ የጉራጌው፣ የአኝዋኩ፣ የደቡብ፣ የጋምቤላ፣ የኦጋዴን፣ የትግራይ፣ የሁሉም ብሔረሰብ 25 ዓመት የግፍና መከራ ዘመን መሠረቱ ወያኔ እንጂ ሌላ አለመሆኑን ትኩረት ሰጥቶ የአንዱ ትግል ከሌላው ይቀናጅ ዘንድ ጥረት እንዲደረግ እናሳስባለን። ለዚህም "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" የሚቻለንን ሁሉ እናደርጋለን።

***ኢትዮጵያዊነትን ማጎልበት፦*** ከወያኔ ውድቀት በኋላ ኢትዮጵያ ሁሉንም ብሔር/ብሔረሰቦች በእኩልነትና በዴሞክራሲያዊ መንገድ አቅፋ የዘር ፖለቲካ ለኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ቦታውን መልቀቅ ስለሚገባው የምናነጣጥርበት የሽግግር መንግስት በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር የተመሠረተ ይሆን ዘንድ ትኩረት መስጠት

***የወያኔ መውደም፦*** ወያኔ ለአለፉት 25 ዓመታት በያንዳንዱ ቤትና ዜጋ ላይ ያደረሰው ግፍና መከራ ቤቱ ይቁጠረው። ወያኔ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ደም ተቃብቷል። ወያኔ የሀገርና ሕዝብ ሀብት እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ ዘርፏል ለባዕዳን ኃይሎች አሳልፎ ሰጥቷል። ይህ በሀገርና በሕዝብ ላይ የመጣ አሸባሪ አገዛዝ መወገድ አይደለም ወደ ብልሹ የታሪክ መቃብር መከተት ግድ የሚለው ለኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነት ለሕዝቧ አንድነት ሲባል ነውና የተጀመረው ትግል ወያኔን ሳይቀብር ከተሸራረፈ ውጤቱ ሽንፈት ይሆናልና አሁንም የተከፈለው መስዋዕትነት ተከፍሎ በሕዝብ ድል ትግሉ መጠናቀቅ ይኖርበታል።

መብትና ነፃነት የሕይወት መስዋዕትነትን ያስከፍላሉና የወያኔን ገዳይነትና ጨካኝነት ሳይዘነጉ ለወሳኝ ፍልሚያ በተቀነባበረ መልኩ መዘጋጀትና ወያኔ ፋታ ሳያገኝ በሁሉም አቅጣጫ ማጣደፍን ይጠይቃል።

**<u>ከአለፈው መማር፦</u>** ወያኔ የተሸነፈበትን የ1997 ዓ.ም. ምርጫ በዘዴና በማታለል ሊካሄድ የነበረውን የ"ሙት ቀን አድማ" አሰርዞ በማግስቱ መለስ ዜናዊና አጋሮቹ በተቃዋሚውና በሕዝቡ ላይ እንዴት እንዳላገጡ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነውና ይህ ጨዋታ ዛሬ ሊደገም አይገባውም። በወቅቱ ሊደረግ የታሰበውን የ"ሙት ቀን አድማ" በተቃዋሚዎች ደካማ ጎን በመጠቀም እንዲከሽፍ ካደረጉ በኋላና በወቅቱ የተቀሰቀሰባቸውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አቀዝቅዘው ፋታ እንዳገኙ ወድያውኑ የተቃዋሚ መሪዎችን በሙሉ እስር ቤት ከተቱ። አሁን

ማ ሊጮህ! የውጭ መንግሥታትም "በርቱ!" አሏቸው እንጂ ማን ዞር ብሎ ተመለከተና። እና? እናማ ይህን ስህተት የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደግመውም። ወያኔን እጅግ አውቆታልና። በቀጣይነትም በተለይ ወያኔ በአዲስ አበባ ሙሉ በሙሉ በመሸነፉ ነዋሪውን በኑሮ እየቀጣው፣ ከአካባቢው እያፈናቀለው ያለ ቂመኛ አገዛዝ መሆኑን የተገነዘበ ነገ በተለይ ኦሮሞ እና አማራ ልጆች ላይ ሊደርስ የሚችለውን መከራ መገመት አያዳግትም። ወያኔ ምንጊዜም አይታመንም፣ ተንኮለኛና ቂመኛ ነውና መውደም! ብቻ ያለበት አገዛዝ ነው።

ዛሬ በተነሳው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ወያኔ የሚያደርገው ግራ ገብቶታል። የሕዝብ ማዕበል ቀላል አይደለምና። ኢሬቻ ክብረ በዓል ላይ የተገኘው በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ወያኔ እንዳበቃለት ጠቋሚ ነው። የጎንደር ነዋሪ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጥያቄው በወልቃይት ወደ ጎንደር በመመለስ የሚያቆም አይሆንም። መጨረሻ ሰዓት ላይ "የደሞዝ ጭማሪ አድርጌሃለሁ፣ የነዳጅ ጭማሪውን አንስቻለሁ፣ ሴክተር ራቭውን ሰርዣለሁ" ለስዩመ እግዚአብሔር ዓፄ ኃይለሥላሴም እልሆነም እንኳን ለዘረኛውና ለገዳዩ የወያኔ መንግሥት።

ይህ ሕዝባዊ ንቅናቄ በምንም መልኩ በአንዳንድ ሸርፍራፊ መልሶችና ወያኔን ያካተተ የሽግግር መንግስት መቋቋም በሚያልሙ ወገኖችና ባዕዳን ኃይሎች ጥምር ተንኮል መኮላሸት እንደሌለበት "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" አበክረን እናስገነዝባለን።

__*ለታጋይ የፖለቲካ ኃይሎች፦*__ በሀገር ቤትም በውጭው ዓለምም ለአላችሁ የወያኔን አገዛዝ ለምትፋለሙ የፖለቲካ ድርጅቶችን ጨምሮ ለብዙሃን ድርጅቶች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ምሁራን፣ ሴቶች፣ ወጣቶችና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች በሞላ ዛሬ በወያኔ አገዛዝ ሕዝባችን ላይ እየተፈጸመ ያለው ዕልቂት እጅጉን ይሰማናል፣ ያንገበግበናል። ይህንን ቃላት ሊገልጹት የሚያቅተውን መንግስታዊ አሸባሪ ቡድን ወደ መቃብር ለመክተት እጅግ ትልቅ ትንሽ ነገር ይጠበቅብናል። ልዩነቶችን ይዞ በጋራ መንቀሳቀስ። ልዩነቶችን በፀጋ ተቀብሎ ለሚረግፈው ሕይወት ዕምባ መርጨት ሳይሆን እጅ ለእጅ መያያዙ ሀገር ቤት ሆ! ብሎ ለተነሳው ሕዝባችን ብርታትና ኃይል ነውና በአንድ ጥላ ሥር ጊዜያዊ መሰባሰቢያ አጀንዳ መነደፍ ይኖርበታል። ቀጣይ የኢትዮጵያ መንግሥት "እኔ ነኝ" ባይ ሊኖር ከቶም አይገባም። "ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል" እንዲሉ በ1966ቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ቀዳዳ ደርግ ገብቷል፣ የደርግ አገዛዝ የፈጠረው ምሬት የፈለገው ይምጣ ተብሎ ለዘረኛው ወያኔ ሀገሪቷ ተዳርጋለች። ይህ ከቶም ሊደገም አይገባውም እንላለን። የታሪክ መደጋገም አይደለም ድግምግሞሽ ሊያበቃ ይገባል። የሀገራችንን ኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ወሳኞች ባዕዳን ኃይሎች እንዳልሆኑ ሊገባን ይገባል። በአንድ ቀን ያለቀውን የኢሬቻን ዕልቂት እንኳ ሊዘግቡ ያልከጀሉ የዜና አውታሮች የታዘብናቸው በርካታዎች ናቸው። ለሀገራችን ያለነው እኛውና ሕዝባችን እና እኛው ብቻ ነን።

በሀገሪቷ ለተጋጋለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እኔ ሸዌ፣ እኔ ጎንደሬ፣ እኔ ጎጃሜ እያልን ከተበጣጠስንላቸው አመቺው ለወያኔና ለባዕዳን ኃይሎች ነውና ሁኔታዎች ቢያስገድዱም ወደ ወጥመዳቸው እንዳንገባ እንጠንቀቅ። በየአካባቢው የተጀመረው የአማራው፣ የኦሮሞው ትግል

በጋራ ይቀናጅ ዘንድ ታጋይ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ አንድ መድረክ ለመምጣት እራሳችንን ማሳመን ይጠበቅብናል። ይህን ማድረጉ ትግሉን እጅግ ይጠቅማል፤ የወያኔንም ውድቀት ያፋጥናል እንላለን። ካልሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ አነሳሽነት፣ ከብሶቱ ሙቀት ፍላት የተነሳ አይቶንና ታዝቦን የጀመረውን ተጋድሎ በትግሉ በተሰዉ ልጆቹ መቃብር ሥር ወያኔን ሳይቀብር ወደ ኋላ አይልምና የዚያ ጊዜ ለሥልጣኑ አለን ባዮች ልናፍር ይገባናል።

***<u>ለትግራይ ሕዝብ፦</u>*** ወቅቱና ጊዜው በማስገደዱ በተጨማሪም ያለው የወያኔ አገዛዝ የትግራይን ኅብረተሰብ መነገጃ አድርጎታልና መጠነኛ ማሳሰቢያ መስጠቱ ያስፈልጋል። የትግራይ ኅብረተሰብ የወያኔን ዕኩይ ተግባር ከማንም የበለጠ ቢረዳም ምላሹ ዝምታ አይደለም። በወገኖቹ ለሚፈሰው ደም እየደረሰ ላለው ግፍና መከራ ድምጹን ማሰማት ይኖርበታል እንላለን። ይህች ሀገር ዛሬም ነገም በሁሉም ዜጎቿ የጋራ ጥረት ትኖራለች። ታሪክ ነውና ለልጆቻችሁ ታሪካችሁ በበታኝነት፣ በገንጣይነት፣ በዘረኝነት፣ በገዳይነት፣ በመሠሪነት ሀፍረት እንዳያወርስ ድምጻችሁን ማሰማት ይጠበቅባችኋል።

በ"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"ም ወያኔ ስንል ህወሀትን ማዕከል አድርጎ ያለውን የኢሕአዴግ አገዛዝ እንደሆነ እንዲሠመርልን እንወዳለን። በዚህ 25 ዓመት የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ አብረው ያሉ የወያኔ አጋር ድርጅቶች በሙሉ ለተፈጸመው ሀገር ማጥፋትና ሕይወት ቀጠፋ ተጠያቂዎች መሆናቸውን አጉልተን እናስቀምጣለን።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ

**<u>ማሳሰቢያ ፡</u>**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" የመጀመሪያ ቅጽ ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ንቅናቄ" በቅርቡ መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com